# የቅድሥት ማርያም አማላጅነት፣

(ጸጋ እግዚአብሄር ከመምህር ቀለም ወርቄ ኪዳነማርያም 1996)

አማላጅነት ማለት በስዋስዋዊ ትርጉም ማስታረቅ ማስማማትና አንዱ የሌላውን ሃሣብ እንዲቀበለው ማድረግ ነው። በምሥጢር ትርጉም የም እመናን የጸሎታቸው መስላልና የእግዚአብሄር የስጦታው ማስተላለፍያ መንገድ መሆን አማላጅነት ይባላል። እንደ ቅዱሥ መጽሃፍ ምስክርነት የእግዚአብሄር ስራ በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ይፈሰማል። እነዚህም 1. ያለ ምክንያት (እምኀብ አልቦ) 2. በምክንያት (ግብር እምግብር)

1. ያለ ምክንያት (እምኀብ አልቦ)

እግዚአብሄር በሥልጣኑ በማዘዝ ብቻ የፈቀደው ሁሉ ማድረግ የሚችል ስለሆነ (ሉቃስ 1፡37፤ ዘፍጥረት 18፡14) በቃሉ ብቻ ይሁን እያለ የስራውና በሰዎች አስተሳስብ ደረጃ በእግዚአብሀር ተእዛዝ ሆነ ከማለት በስተቀር ከዚህ መጣ ብለን ምክንያት ልንሰጠው የማንችለው አምላካዊ ሥራ ሁሉ ያለምክንያት የተስራ ስራ ይባላል። “እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ” (ዘፍጥረት 1፡3) “...ነገር ግን ቃል ብቻ ተነገረ ብላቴናዬም ይፈወሳል...እየሱስም ለመቶ አለቃው አለው ሂድና እንዳማነህ ይሁንልህ አለው። ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈዋሰ። (ማቴዎስ 8፡8 እና 13) ሰማይንና ምድርን ከባዶ ነገር የፈጠረና የመቶ አለቃውን ልጅ በቃሉ ብቻ የፈወሰ “ኤልሻዳይ” (ሁሉን ቻይ) እግዚአብሄር ከባዶ ነገር ተአምር መስራት ይችላል።



2. በምክንያት (ግብር እምግብር)

እግዚአብሄር አዲስ ፍጥረት ለመፍጠርና እርሱ ለሚፈልገው ዓላማ ወደ ፍጥረቱ ለመድረስ በፊት የሠራው ፍጥረቱን መሣርያ ያደርጋል። ከቀደመው ፍጥረት አዲስ ፍጥረት ይፈጥራል፤ በፍጡራን በኩል ወደ ፍጡራን ይደርሳል። አዳምን ለመፍጠር በመጀመርያ የፈጠረውን አፈር መሣርያ አደርጉአል። “እግዚአብሄር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው” (ዘፍጥረት2፡7) ለዓይነ ስውሩ ብርሃንን ለመስጠት ጭቃንና የሲሊሆምን ውሃ መሣርያ አድርጉአል። (ዮሃንስ9፡6) “ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ በምራቁም ጭቃ አድርጎ የእውሩን ዓይን ቀባና ሂድና በሲሊሆም መጠመቅያ ታጠብ አለው” በደረቅ የሙሴ በትር ውሃን ከፍሉአል አንተም በትርህን አንሣ እጅህንም በሙሴ በትር፤ በጭቃና በሲሊሆም ውሃ ሃይሉን ያስተላለፈ በእሜቤታችን፤ ቅዱሳን መላእክት፤ ቅዱሳን ሳድቃን ሰማእታት ሀይሉን ያስተላልፋል። የሙሴን በትር ለሥራው ምክንያት ማድረጉ ሰማይንና ምድርን በቃሉ ብቻ መፍጠሩን እንዳልተቃወመው ሁሉ በ አማላጆች በኩል ጸሎታችንን

መቀበሉ በቀጥታ እሱ መቀበል መቻሉን አይቃወምም። ወደ ሰው አማላጅ ስንልክ የለክንበትን ሰው የበለጠ ማክበራችን እንጂ የሰውየውን ክብር መቀነሳችን አይደለም። እንደዚሁም ጸሎታችንን በአማላጆች በኩል ማቅረባችን የአምላካችንን ክብር መቀማትና ለሌላ መስጠት ሳይሆን የበለጠ ማክበራችን ነው።